ይህ ጽሁፍ የዛሬ ዓመት በዚህ ወር፣ **03-03- 2015** አንዳንድ የታውቁ አጭበርባሪዎች፣ በልማትና ሥርዓቱን በመደገፍ ሽፋን፣ የሕዝብ ገንዘብ ሊዘርፉ ካኮበከቡት ውስጥ በግል ስለሚታወቁ **"አስመሳይ አልሚዎች"** የማያቋቸውን የዋህ ወገኖች ለማስጠንቀቅና ሥርዓቱም ሊደግፋቸው ቃል የገባላቸው **ሰባ ዓምስት በመቶ ካፒታል** የሕዝብ ገንዘብ ስለሆነና እንደ ዜጋ ስለሚመለከተኝ፣ ይቺን አጭር ዘገባ ጽፌ ስጋቱን ለማካፈል ነበር የሞከርኩት፡፡
ዛሬ በዓመቱ ችግሩ ደርሶ በየፓልቶኩ ስለዚህ ጉዳይ ሞቅ ያለ ክርክር እየተካሄደበት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ያኔ ጽሁፉን **"እንዲሆን የምትፈልገውን ምኞት ነው የጻፍከው"** ብለውኝ ከተቃወሙኝ ውስጥ የተወሰኑትና አንዳንድ ወዳጆቼም ጭምር አሁን ጽሁፉን ፈልጌ እንድልክላቸው በጠየቁኝ መሠረት፣ ለጥቂቶቻችሁ እንደገና ስልክ አዲስ እንዳይመስላችሁ በማሳሰብ ነው፡፡
**"በበይዎች መሃል የሚካሄደው አለመስማማት ለተበይዎች ይበጃል"** እንደሚባለው፣ ይህ አሁን የደረሰው ችግር ዘርፈ ብዙ ቢሆንም፣ ለሥርዓቱ ይበልጥ ታማኝነትን አስመስክሮና ተቀናቃኝን ፈንግሎ በማስወገድ አመራሩንና ጠቅልሎ፣ ካፒታሉ የሚፈጥረውን የሥራ ዕድል ተጎናጽፎ የየዋህ አልሚዎችን ንብረት ለመዝረፍ የሚካሄድ ትንንቅ ሲሆን፣ በዚህ መሃል፣ ያዋጡት ንብረት ቀልጦ እንዳይቀር፣ የተጀመረው ዕቅድ እንዳይፈርስ፣ የተቃዋሚው ክፍል ሁኔታውን እዳይጠቀሙበት ያቀፈ ሥጋት ጭምር ያለበት ነው፡፡ በእርግጥ የተቃዋሚው ክፍልም ሲያስጠነቅቅ የነበረው አደጋ ደርሶ በመታየቱ፣ ሁኔታውን ተጠቅሞ ይበልጥ ትምህርት ሊሰጥበት እየሞከረ ብቻ ሳይሆን፣ ሥርዓቱን በፓልቶክ ውስጥ በመቃወም የሚታወቁ የነበሩ ግለሰቦች ጭምር፣ ችግሩን ለመፍታት በዳኝነትና በአማካሪነት ጭምር በሁለቱም የሥርዓቱ ደጋፊዎች ተቀባይነት አግኝተው " የቸገረው እርጉዝ ያገባል" የሚባለው ተረት በተግባር እያየነው ይመስላል፡፡
ጽሁፉ ያኔ በችኮላ በደንብ ሳላርመው የተሰራጨ ስለነበርና የወርድ ዶኪሜንቱን ላገኘው ስላልቻልኩኝ፣ ፒዲኤፉ ላይ ለሚታዩት አንዳንድ ስህተቶች በቅድሚያ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡

**ካስመሳይ ‵‵አልሚ‵‵ ሁሊጋንኖች እንጠንቀቅ ነው የተባለው!!**

**ብስራት ኢብሳ (ሆላንድ)** **03-03-2015**

በእስፖርት ዓለም ሁሊጋንዝም የሚታወቀው በባዛንቲያን ዘመን ከ 532 አካባቢ ጀምሮ ቢሆንም፣ በተለይ በምዕራብ አውሮፓ የተስፋፋው በሃምሳዎቹና በሰባዎቹ ውስጥ እንደነበር ታሪክ ያረጋግጣል፡፡ ይህ በአፍራሽነቱና በአውዳሚነቱ በስፋት የሚታወቅ ከእግር ኳስ ግጥሚያ ጋር የተያያዘ፣ ጥቂት ወሮ በሎች እንደ ብዙሃኑ እስፖርት አፍቃሪ፣ እራሳቸውን የሚቆጥሩና፣ ሳይሆኑም አስመስለው በመደባለቅ፣ ከፍተኛ የውድመትና ሕገ ወጥ ተግባር የሚካሄድበት ስብስብ ነው፡፡

በመሠረቱ የሚወዱትን ቡድን ደግፎ የክለቡ ትጉህ አባልም ይሁን ተራ ደጋፊ ተኩኖ፣ ከቁሳቁስ እስከ የሞራል ድጋፍ መስጠት፣ መለያ ዓርማውንና መሃልያውን በመልበስ ማበረታት፣ የድሉን-ደስታም ሆነ የሽንፈቱን-ሃዘን መካፈል፣ የጫወታውን ሕግና የዳኛውን ውሳኔ እስካከበሩና እና እስከ ተቀበሉ ድረስ ከሁሊጋኒዝም ጋር ምንም ግንኙነት ስለሌለው ጤናማ የእስፖርት አፍቃሪናትን ነው የሚያሳየው፡፡

የእስፖርት ሁሊጋንዝም ከላይ ከጠቀስኩት የተለየ ነው፡፡ ሁሉም ሁሊጋን ብዙ የሚያመሳስላቸው ባሕሪያት ቢኖርም፣ ሁሉንም በአንድ ቅርጫት ውስጥ ላለመክተት፣ የታዘብኩትን ሁለት መሠረታዊ ልዩነቶቻቸውን ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

**የመጀመርያዎቹ** ሁሊጋኖች ዋናው ግባቸው፣ የሚደግፉት **ቡድን ምንም አይነት መንገድ ተጠቅሞ እንዲያሸንፍ ነው፡፡** የቡድናቸው ሽንፈት በራሳቸው ላይ እንደደረሰ ጥቃት አድርገው ስለሚወስዱት የዳኛውን ውሳኔ የመስመር አራጋቢውን ምስክርነት አይቀበሉም፡፡ በቡድን ስለሆነ የሚያስቡትና የሚመሩት፣ ለደረሰባቸው ችንፈት ማካካሻ ቢችሉ በኀብረት ኳሱ ሜዳ ገብተው አሸናፊውን ቡድንና ዳኛውን ከመደብደብ አይመለሱም፡፡ ይህ ካቃታቸው ብስጭታቸውን ለማብረድ በመንገዳቸው ላይ የሚገጥማቸውን ንብረትና መንገደኛ ላይ በቡድን ጉዳት በማድረስ‵‵ያካክሳሉ‵‵፡፡ ወይም ከተቃራኒው ቡድን ደጋፊዎች ጋር ቀጠሮ ይዘው ቡጢ በመግጠም፣ በኳስ ሜዳ ያጡትን ዕድል ለማካካስ ይደባደባሉ፡፡ ብዙዎቹ ስለሚፈሩና ትንሽ የተረፈቻቸው ‵‵ኅሊና‵‵ እንዳትቆረቁራቸው በገፍ አልኮልና፣የሚያጃጅል ዕፅ ለመደፋፈር ይወስዳሉ፡፡

**ሁለተኛዎቹ** ሁሊጋኖች ዋናው ግባቸው **ዝርፊያና ሌብነት** ነው፡፡ ለዚህ ዓላማቸው ቀውሱንና ግር ግሩን በጣም ይፈልጉታል፡፡ ከእውነተኞቹ የእስፖርት አፍቃሪውች በላይ ኳስ ሜዳ ሄደው ይጮሃሉ፣ ያዳምቃሉ፡፡ የተቃራኒውን ደጋፊ ይሰድባሉ፣ ሊደባደቡ ይጋበዛሉ፡፡ አንባጓሩ እንዲፈጠር ክብሪት የሚጭሩ፣ ቡድኑን ወደ ግጭት የሚገፋፉ ዋናዎቹ እነዚህ ሁለተኞዎቹ ናቸው፡፡ ለዚህ ሁሉ ዋናው ምክንያታቸው ቀውሱን ተጠቅመው ሱቅ ሰብረው ለመዝረፍና፣ ተራ የሌብነት ተግባር ለመፈጸም ነው፡፡ እነዚህ በበጎች መሃል የተደበቁ ተኩላዎች ቀውሱና እረብሻው በበዛ ቁጥር፣ በእነእሱ ላይ ትኩረት ስለማይኖር ዝርፊያቸውን በቀላሉ እያከናወኑ፣ በብዙሃን የእስፖርት ደጋፊ ስም ወንጀል ይፈጽማሉ፡፡

ሁለቱ ክፍሎች የሚመሳሰሉበት መንገድ፣ የጨዋታውን ሕግ እና የዳኛውን ውሳኔ ባለመቀበል ነው፡፡ ሁሉም እንደሚያውቀው፣ በዛሬው የሰለጠነ ዓለማችን እንኳን የእግር ኳስ እስፖርት ጨዋታ ቀርቶ፣ ቡጢና ጦርነት እንኳን ዓለም አቀፋዊ ስምምነት የተደረሰበት የራሱ ሕግ አለው፡፡

የቦክስና፣ የካራቲ፣ ድብድብ ግጥሚያ ስለሆነ የተፎካካሪውን ጆሮ ነክሶ ማሸነፍ የጨዋታው ሕግ አይፈቀድም፡፡ ለቡድኑ ሽንፈትን አስከትሎ፣ ከእድሜ ልክ ጨዋታ ያሰርዛል፡፡ በክለቡ ላይ ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣት ያስከትላል፡፡ የጦርነትም እንደዚሁ በውጊያ መሃል በሚደረግ ጊዜያዊ የተኩስ አቁም ስምምነትን መጣስ ዓለም አቀፋዊ ውግዘት ብቻ ሳይሆን፣ የኢኮኖሚ ማዕቀብ ቅጣትን እንደሚያከትል ይታወቃል፡፡

ልክ እንደ እስፖርት ሜዳው፣ በአገዛዙም ይሁን በተቃዋሚው ሰፈር  የጨዋታውን ሕግ  መረዳት የሚቸግራቸውና አውቀውም መቀበል የማይፈልጉ አሉ፡፡  ያልገባቸውን ትተን፣ በተለይ እነዚህ ገብቷቸው ነገር ግን መቀበል የማይፈልጉ ጮሌ የፖለቲካ ሁሊጋኖች፣ ዋነኛ የተደበቀ ዓላማቸው ወደ ፖለቲካው ሰፈር ተጠግተው፣ ሐገር ወዳድ መስለውና አዘንግተው፣ ዘርፈው አምታተው ለመክበር ነው፡፡ ሐገር፣ ሕዝብ፣ እድገት፣ ልማት፣ምርጫ.... ወዘተ ለሽፋን እንጂ የሚጠቀሙበት  ከልባቸው አያምኑበትም፡፡ ልክ እንደ ሁለተኛዎቹ የእስፖርት ሁሊጋኖች፣ ግጭት፣ እረብሻ፣ ግር ግር መኖር፣ ታዛቢ እነሱ ላይ እንዳያተኩር ስለሚረዳ፣ ቀውሱን ማያያዝና ማቀጣጠል ተመሳሳይ ባህሪያቸው ነው፡፡ በሬ መንታ ወለደ አይነት የሃሰት ወሬ መንዛት ልዩ የተካኑበት ስልት ነው፡፡ ያልገባቸውን የዋህ ሐገር ወዳዶችን በመቀስቀስና ከጎናቸው በማሰለፍ በራሳቸው ላይ የሚያንዣብበውን የፍርሃት ድባብ አጠገባቸው ያሉት እንዲጋሩት ጠልፈ ያስገባቸዋል፡፡ ያልተባለውን ተባላችሁ በማለት በቡድናቸው ውስጥ ሽብር ፈጥረው፣ ትርምሱ ሲጋጋል በነሱ ስር ሊደበቁ ይጥራሉ፡፡ የማኅበረ-ሰባችን ኅብረት በተዳከመበትና፣ ትንሽ ተከፋፍለን ክፍተት በሚፈጠርበት ወቅት እቅዳቸውን ለማከናወን የተመቻቸ ሁኔታ ስለሚፈጥርላቸው፣ ይህንን ሁኔታ ለማምጣት መጀመርያ አንድ ጎራ መርጠው ወገኖቻችንን ለመከፋፈል ተግተው ይሰራሉ፣ ወይም ያ እስከሚመጣ አድፍጠው ይጠብቃሉ፡፡ ሁኔታው እስኪመቻችላቸው ጮክ ብለው በሕዝብ ስም እየማሉና እየተገዘቱ የተመልካችንና አዳማጭን ቀልብ ለመሳብ ይጥራሉ፡፡

የትም ስፍራ ``ግንባር ቀደም ሆነው`` ልታይ ልታይ ያበዛሉ፡፡ ከዚያ ሁሉ ቲያትር ጀርባ ግን የራሳቸው የተደበቀ በሌብነት የመክበር አጀንዳ አስቀምጠው ነው፣ ገንዘብ ገንዘብ የሸተታቸው አካባቢ የሚያነፈንፉት፡፡ ይሉኝታ፣ ርህራሄ፣ ምን ያስከትልብኛል ብሎ የሚያስብ የማመዛዘኛ እዕምሮ የላቸውም፡፡ ጥቅም ከተገኘ ያመሹበት አያድሩም፣ ያደሩበት አያመሹም፡፡  በእርግጥ እንደዚህ እንዲያምታቱ በተደጋጋሚ ሲያታልሉን፣ እንኳን ደህና በሰላም መጣችሁ እያልን፣  ዋንጫ አሸንፈውልን እንደተመለሱ በእቅፍ አበባ እጃችንን ዘግተን ሁሌ ለምንቀበልናቸው፣ የኛም ስህተት አለበት፡፡

ትላንት በተቃዋሚው ጎራ፣ ስንት የተከበሩና አንቱ የተባሉ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችን ሲያጅቡና ሲያጃጅሉ የነበሩ፣  ስንቱን መኳንንት ከእንቅልፋቸው እያስቀሰቀሱ፣ ሱሪ እንኳን ማጥለቂያ ጊዜ ሳይሰጡ ከነፒጃማቸው በጥያቄ እያጃጃሉ እንዳላንበዛብበዙ፣ ከወዲያ ወዲህ ስንት ጊዜ አክሮባት እየሰሩ ሲገለባበጡ እንዳልቆዩ፣ በርግጥ ታዛቢ ብቻ ሳንሆን ብዙዎች አጃቢዎችም ነበርን፡፡ ``የዛሬን ችግር ይሸፍኑልን እንጂ`` ትላንት የት ሆነው ምን ይሉ ነበር? ዛሬስ እኛን ላለመከዳታቸው ምን ዋስትና አለን?`` ብለን ላለመጠየቅ፣ ለራሳችን ቃል የገባን ይመስላል፡፡ የእውነት መቀየራቸውን ገና እራሳቸው እንኳን ሳያጣጥሙት፣ እኛ ልናረጋግጥላቸው እንሽቀዳደማለን፡፡ የሚመዘኑት በሚሰሩት ተግባር ሳይሆን፣ በምላሳቸው ጥንካሬና፣ በሚያጃጅሉን ቧልት ነው፡፡ ቁም ነገር ከመወያየት ይልቅ፣ ለመደበርያ ስድብ፣ ብሽሽቅና ስሜታዊ በሆኑ ነገሮች ዙርያ ክፍል ሞልተው ሲያጃጅሉን እንደ ከሰል ምድጃ ከበን እየሞቅንናቸውና  እያሚሚቅን መፋዘዝን የመረጥን እኛም ጭምር ነን፡፡

እንደ እነዚህ አይነት ወስላቶችን እያወቁ እንደ መናጆ የሚጠቀሙባቸው አንዳንድ የተቃዋሚም ድርጅቶችም ሆኑ አገዛዙ፣ ለጊዜው ``ትርፍ ያተረፉባቸው`` ይመስላቸውል እንጂ፣ ዓመል ነውና፣ ነገ የተሻለ ሲያገኙ ወይም፣ የወጠኑት ዕቅድ ሳይሳካ ቢቀር፣ ከማንም በላይ ጠላት ሆነውና ከተቃራኒው ጋር እንደገና ተሰልፈው ከኋላ የሚተኩሱባቸው እነዚሁ ከሃዲዎች ናቸው፡፡ አክሮባቲስቶችን የሚያስንቅ የመገለባበጥ ችሎታቸውን እያየን እንዳላየ ሆነን ከማለፍ የፈየድነው ነገር ስለሌለ የራሳችንንም የሃላፊነት ድርሻ መቀበል ይኖርብናል፡፡ እንደ የኳስ ሜዳዎቹ ሁሊጋኖች ሁሉ፣ ``የፖለቲካ ጨውታን ሕግ`` መረዳት ከመቸገራቸውም በላይ፣ ለሆዳቸው ሲሉ ስለማይቀበሉ፣ በዚህም ሂደት ውስጥ በመቀላቀል የሚፈጥሩት ውዥንብርና፣ የሚያደርሱት ጥፋት ትግሉን ከማዳከምና ውዥንብር ከመንዛት ያለፈ ምንም የረባ የሚፍይዱት ነገር የለም፡፡

እነዚህ በፖለቲካ፣ በልማት፣ በእምነትና በእስፖርት... ወዘተ አካባቢ እያደቡ፣ ለበጎ ነገር በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ፣ ከሃቀኞቹ ጋር ተመሳስለው፣ ዘርፈውና አጭበርብረው በሕዝብ ንብረት ሊከብሩ፣ በግልጽ ካለፈ ተግባራቸው የሚታወቁ ወስላቶችን ማጋለጥና፣ ማስጠንቀቅ፣ ወገናዊ ግዴታ ነው፡፡ እነዚህ ዘራፊዎችም ሆኑ ማንነታቸውን አውቀው ሊጠቀሙባቸው ብቻ የፈለጉ ክፍሎ፣ እንደዚህ አይነት የማስጠንቀቂያ ደውል መስማት እቅዳቸውን ስለሚያበላሽባቸው፣ ይህ ወደ ወገኖቻችን ጆሮ እንዳይደርስ፣ ከበሮ እየደለቁ፣ ነጋሪት እየጎሰሙና ጡሩንባ እየነፉ አብዋራው እስከሚጨስ ማንኛውንም ምክንያት እያቀረቡ ለማከላከል እንደሚጥሩ ግልጽ ነው፡፡ ይህንን የመሳሰለ ጉዳዮችን በተመለከተ፣ሰሞኑን በመረጃ ላይ የተደገፈ አስተያየት ለማቅረብ፣ ካለወትሮዬ የተለያዩ የፓልቶክ ክፍሎችንና፣ ድኅረ-ገፆችን ስከታተል ነበር፡፡

ይህንን ዳሰሳዬን የሚያውቅ አንድ ወዳጄ፣ በቅርቡ በአንድ የፓልቶክ የውይይት ክፍል ይካሄድ የነበረውን ውይይት እንድሰማ በጣም ገርሞት እየሳቀ ስልክ ይደውልልኝና ገብቼ ሳዳምጥ፣ እንደ አጋጣሚ ተናጋሪውን በደንብ የሚያውቀኝና የማውቀው ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው የውሸት ውድድር ቢዘጋጅ ቢያንስ ከሚኖርበት ከተማ አንደኛ ይወጣል ብዬ ሁሌ እወራረዳለሁ እያልኩኝ እቀልድ ነበር፡፡ አሁን ግን የእውነት እየሆነ የመጣ መሰለኝ፡፡ ክፍሉ የፕሬስ ማብራሪያ ሊሰጥ እንደቀረበ ትልቅ ባለስልጣንና፣ መግለጫውን ለመስማት ከበው እንደሚጠብቁት ዜና የጠማቸው ጋዜጠኞችን መስሏል፡፡ እስከሚጀምር፣``ገብቷል፣ ሊቀርብ ነው`` እየተባለ እንደባለስልጣኖቹ ትንሽ አስጠብቆና ደጅ አስጠንቶ ነበር ወደ መናገርያው የቀረበው፡፡ ግለሰቡ ብቻውን ``ሰዎችን በማስፈራራትና፣ በማጭበርበር ተጠርጥሮ`` እንደተከሰሰ በስፋት ቢታወቅም፣ ይህንኑ ከራሱ አንደበት ጭምር ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ዘርዝሮ ነግሮን፣ በሁለተኛ ዙር ሲመጣ የመጀመርያውን እረስቶት ይሁን አያስታውሱም ብሎ እንጃ፣ የሚታደምበት ክፍል ጨምሮ ከነአባላቱ በአሸባሪነት እንደተከሰሱ ሲዋሽ አዳምጨዋለሁ፡፡ በጣም የገረመኝ በክፍሉ ውስጥ የነበረው ታዳሚ፣ አዝነውለት ይሁን አምነውት እንጃ እንደተሳሳተ ሊነግረው ወይም ሊጠይቀው እንኳን የሞከረ አንድም ሰው አልነበረም፡፡ ደጋግሞ የተናገረው ``የከሰሱኝን አውቃቸዋለሁ፣ እነዚህ ሥራፈቶች በጡረታና በመንግሥት ገንዘብ የሚኖሩ ናቸው`` ሲል፣ አንድ ጎበዝ ታዛቢ ብቻ፣ እንደዛ ማለት ጥሩ እንዳልሆነ፣ ብዙ በዚህ አይነት እየተዳደሩ  ቤተሰባቸውን በሥነ ሥርዓት የሚከባከቡና ሐገራቸውን የሚወዱ ሰዎች ስላሉ ብዙ ሰው ታስቀይማለህ`` ብሎ ሲወቅሰው ከሰማሁት ታዳሚ በስተቀር ማንም ስህተቱን ሊነግረው የሞከረ አልነበረም፡፡ በእርግጥ አብዛኛው ታዳሚ በዝምታ እያዳመጠ መታዝብን የመረጠ ሲመስል፣ የቴክስት ጦርነቱ፣ በተለያየ ቀለማት ያሸበረቁ፣ እሰጥ እገባዎች ከሁለት አቅጣጫዎች ይሰነዘሩ ነበር፡፡

ጭፍን ደጋፊዎች ወይም የሚነግራቸውን በሙለ እንደወረደ ተቀብለው የሚያምኑት መሰሉኝ፣ ተናጋሪው ጉንፋን ቢጤ ይዞት ስለነበር መሰለኝ፣ በተደጋጋሚ በሳለና ባስነጠሰው ቁጥር አበባ ሲበትኑለት፣ ባዲሱ የፓልቶክ ባህል ``ይማርህ`` ማለት ይሆናል ብዬ አሰብኩና፣ ቦኋላ የሰውዬውን ጸባይ ሳስታውስ፣ ምናልባት ``እውነት ሲናገር ነው፣ ሰው የሚያስነጥሰው`` የሚለውን አባባል በሚያምኑበት ሰዎች ላይ እየሰራ ይሆን ብዬ አሰብኩኝ፡፡ ይህ ግለሰብ እንዴት እንደሚዋሽና እንደሚያጋንን ከጥቂት ዓመታት በፊት እራሴ ላይ ካደረገው ሙከራ ባሻገር፣ በሌሎች ሰዎች ላይ ያደርግ የነበረውን የማምታታት ተግባር ከራሱ አንደበት ጭምር ስለሰማሁ፣ አመሉ እላዩ ላይ ደርቆበት ዛሬም ምንም እንዳልተቀየረ ነበር የተረዳሁት፡፡

(ስለሱ የማውቀውን እዚህ ለመዘርዘር ቦታው ስላልሆነና ፍላጎቱም ስለሌለኝ፣ በተጨማሪም፣ እዛው ክፍል ውስጥ ከራሱ አንደበት የሰማሁት ዜና እውነት ከሆነ? በሕግ የተያዙ ጉዳዮች ስላሉበት፣ ይህን ላለማደናቀፍና፣ ቤተሰቡን እዚህ ማጥ ውስጥ ላለመጎተት፣ ስሙንና ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ ከመግባት እቆጠባለሁ)

ይህ ሰው ከጥቂት ዓመታት በፊት ወደ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ተጠግቶ፣ የአውሮፓ ተወካይ ነኝ ``አገዛዙን እቃወማለሁ`` በማለት በስማቸው ለስልክ፣ በእስር ለተጎዱ ቤተሰቦች፣ ለተቸገሩ .....ወዘተ እያለ ገንዘብ ሲሰበስብና  ካለደረሰኝ ሲቀበል ሳይ ያዘንኩት በሱ ሳይሆን፣ በሱ ላይ እምነታቸውን ጥለውና አስጥለው ታዳሚውን ለማዘረፍ በወኩሉት ላይ ነበር፡፡        ለነገሩ የገንዘቡ ቅጣት እኔንም ቢደረሰኝ፤ አጋጊጠውና ኳኩለው አስቀምጠውት ለነበሩት በወቅቱ ቅሬታዬን ከማስተላለፍ አልቦዘንኩም፡፡

ሰዎች በሂደት ከስህተታቸው እንደሚማሩና እንደሚቀየሩ በመሠረቱ አምናለሁ፡፡ ነገር ግን ይህ ንድፈ ሃሳብ ሁሉም ላይ አይሰራም፡፡ ከማይሰራባቸው ሰዎች አንዱ ደግሞ ይህ ግለሰብ ነው፡፡ ምክንያቱም ስህተቱን መደጋገሙ ብቻ ሳይሆን በሚያጭበረብረው ሥራና በሚጎዳቸው ሰዎች እንዴት እየሳቀ እንደሚደሰት በማየቴ ነው፡፡ ጥቅም ካመጣ ዘመድ፣ ወዳጅ፣ ጓደኛ ብሎ ጣጣ ነገር ብሎ አያውቅም፡፡ ዕቅዱን ወይም ጥቅሙን የሚያደናቅፍበት ከመሰለው፣ እነዚህ እንደ ምሁርና ፖለቲከኛ የሚያስመስልባቸው ጭምብሉ ይገፈፍና፣ እውነተኛ እራሱን ሆኖ፣ ካፉ የሚያወጣቸው አስቃቂ ቃላት፣ እንኳን እዚህ ላይ ልገልጸው ላስበው ይሰቀጥተኛል፡፡ በቅንጅት ውስጥ አብራው መስሏት ትለፋ በነበረች ሴት እህት ላይ፣ ገብንዘቤን አጭበርብሮኛል ብቻ ስላለችው፣ ያን ሁሉ ታዛቢ ሳይፈራ አጸያፊ ቋንቋ ሲጠቀም፣ አጠገቡ ያሉት ``ነግ በኔ`` ብለው ሊጠነቀቁ በተገባ፣ አጫፋሪዎቹ አበባ ሲበትኑለት፣ አንድ ኅሊና ያላት እህት ብቻ ነበረች ``ካሁን ቦኋላ አጸያፊ ቃል አትጠቀም!!`` ብላ በድፍረት የቀረበች፡፡ እኔም አድናቆቴን ለማሳየት ቢያንስ አበባ በትኜላታለሁ፡፡

ያለፉትን ዓመታት እንተወውና በቅርቡ  የሰማሁትን አንድ ታሪክ አሳዛኝ ታሪክ ነግሬያችሁ ልለፍ፡፡ ሰውዬው አሁን የያዘውን ዙር፣ የማምታታት ተግባሩን የጀመረው ገና ከባለሥልጣናት ጋር መተዋወቅ ሲጀምር ነው፡፡ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ እስከ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ሁሉም በእጁ ናቸው፡፡ ስልክና አድራሻቸው ያለኝ የቅርብ ወዳጆቼና የፌስ ቡክ ጓደኞቼ ናቸው ብሎ ሲያወራና ሲያስወራ፣ ለቀጣዩ እቅዱ እየተመቻቸ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡  መጀመርያ በሚኖርበት ሐገር የሚቀርባቸውን አንዳንድ ቱጃር ወዳጆቹ ዘንድ ከሐገር ውስጥ በሰው እያስደወለና፣ ከባለሥልጣን እነደተደወለ በማስመሰል ``ትርፍ ቦታ...ወዘተ እንደነበሮት አላስመዘገቡም፡፡ ለ...ያለተከፈለ ውዝፍ  ያልተስተካከለና ያልተጣራ ጉዳይ አለባችሁ ...ወዘተ`` የሚል  አስደንጋጭ ዜና እንዲሰሙ ያስደርጋል፡፡ ሐገር ውስጥ አንዳንዳን በቢሮክራሲው ችግር የደረሰባቸው እንደሚደውሉለትና ጉዳያቸውን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም እንደሚለምኑት ስለ አንዳንድ ጉዳዮች በሰላሙ ጊዜ ያጫወቱትን ስለሚያውቅ፡፡

ልክ እንደሚጠብቀው ባለስልጣኖች ያውቃል ብለው እነዚህ የዋሆች ይደውሉለትና፣ የሚወጣ የሚወርድበትን ወጪና በእጅ የሚባለውንም ጨማምረው ችግራቸውን ``በወዳጆቹ`` በኩል እንዲያቃልልላቸው ያላቸውን ያራግፉለታል፡፡ በሁለት ስልክ በመጠቀም፣ ከባለሥልጣን ጋር እንደሚነጋገር፣ የሚታወቁ ሰዎችን ስም ጮክ ብሎ እየጠራና  ስለ ጉዳዩን  የሚያወራ እንደሆነ እያስመሰለ በሌላ ስልክ ለባለጉዳዩ እያሰማ ጉዳያቸውን እንደሚያስፈጽም አስመስሎ ይጫወትባቸዋል፡፡ ግለሰቡን ካራቆተ ቦኋላ፣ እንዲህ አይነት ጅብዱ ለሚያዳንቁለት፣ ``ይሄውላችሁ ይህንን ፋራ ይሄንን ያህል .....በላሁት`` ብሎ እንደ ትልቅ ጅብዱ ሊያሳፍረው የሚገባውን ተግባር እይተኩራራ፣ እስከሚያለቅስ ድረስ እየሳቀ መልሶ የረዱትን ሰዎች ያፌዝባቸውል፡፡ ይህ አይነት የማታለል ዘዴ ድሮ ሐገር ቤት ውስጥ በፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ ``ቁጭ በሉ`` በሚባል ስያሜ የሚታወቁ አታላዮች፣ የብዙ የዋህ ሰውችን ንብረት የሚዘርፉበት መንገድ እንደነበር አንብቤያለሁ፡፡ አንድ ጤነኛ አዕምሮ ያለው ሰው፣ ስንት የሥራ ዕድል ያለበት ሃብታም አውሮፓ ሐገር እየኖረ ምንም ቢቸግረው በጉልበቱ ሰርቶ መኖር ሲችል በዚህ አይነት ለመክበር መሞከር ምን አይነት ሞራል ይሁን ሞራ እንዳለው አልገባኝም፡፡

ከዚያም እርቆ ሄዶ ``ዲያስፖራ ተቃዋሚ ነን እያሉ ሐገር ውስጥ የሚገነቡትን ሕንጻ አይተናል፣ ሊስቱ በእጃችን ገብቷል አናርፍ ካሉ?....ወዘተ`` አይነት ዛቻ፤ የአገዛዙን ቀልብ ለመሳብና ውለታ ለማስመዝገብ እንኳን ቢሆን? ይህንን ቃላት መርጦ ለማስፈራርያነት መጠቀም መጀመር፣ ነገ በዚህ መንገድ ደግሞ እያስፈራራ ``ቢዝነስ'' ሊሰራበት? ማመቻቸት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ በፖለቲካ ሽፋን የሚካሄድ  የውንብድና  አካሄድ እደግፈዋለሁ የሚለውን ስርዓት እንኳን አይጠቅምም፡፡ በዚህ አይነት ከሚገኝ የፖለቲካ ጥቅም አደጋው ነው የሚያመዝነው፡፡ እንዲያውም የተገላቢጦሽ አገዛዙን ይበልጥ ሕዝብ እንዲጠላውና በጠላትነት እንዲመለከተው ነው የሚያግዘው፡፡

እሱ ለታዳሚዎቹ ሊያሳምን ይሞክር እንደነበረው፣ ማንም የማመዛዘን ህሊና ያለው የሐገርን እድገትና የወገንን ምቾት የሚጠላ የለም፡፡ ሰዎች ሐገራቸው ስለገቡና ንብረታቸውን ለወገናቸውንና ለራሳቸው ስለረዱ ወያኔ የሚላቸው በፍጹም እንደሌለ እራሱም ያውቀዋል፡፡ ነገር ግን እንደዚህ አይነት አይን ያወጣ ዉሸትና ቅጥ ያጣ ድፍረት ይዞ መቅረብ ታዳሚውንም ከመናቅ የመጣ ይመስለኛል፡፡ እንደዚህ አይነት ነገ የሐገርንና ሕዝብን ጥቅም ለጎዱ የሚችሉ ግለሰቦች፣ ከየትኛውም አቅጣጫ ይሁን የሚመጡት፣ ለእንደዚህ አይነት ዝርፊያና ምንተፋ ሲያኮበክቡ፣ እንዳላየና እንዳልሰማ ሆኖ ማለፍ ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

ይህ የፖ. ሁሊጋን እንዴት አድርጎ ሁለት መቶ አካባቢ የሚጠጉ ያዳሚዎችንና፣ ከአምስትና ስድስት በማይበልጡ ንቁ ተሳታታፊዎች መሃል ተገኝቶ በድፍረት እየዋሸ  ክፍሉን የራሱን ፍርሃት መከላከያ ለማድረግ ሲሞክር አስተውያለሁ፡፡ ከጭፍን የወያኔ ደጋፊዎች ጋር በመደጋገፍ ብዙሃኑን ከጎኑ ለማሰለፍ እየሞከረ ለመከላከያ ሊጠቀምባቸው ብቻ ሳይሆን እንደገና ቀውሱን ሊከብርበት በጥቂት አጃቢዎቹ ቅስቀሳ፣ ``ለጠበቃ`` በሚል ሰበብ ግራ ከገባቸው ታዳሚዎች ኪስ፣ ለሁለተኛ ዙር ገንንዘብ አሰባስበው ሊመነትፍ  ሲያመቻቿቸው አዳምጫለሁ፡፡ በራሱ

ላይ የመጣውን ችግር፣ ክፍሉ ከነታዳሚዎቹ በሕግ እንደተከሰሱ አድርጎ ደረቅ ውሸት ሲዋሽ ብቻ ሳይሆን፣ ክፍሉንም ሆነ እራሱ በፍጹም ሊሆን በማይችል ``በአሸባሪነት`` ክስ እንደተመሥረተባቸው ሲዋሽ ሳዳምጥ፣ ያዘንኩት ይህ ውሸት መሆኑን አውቀው የፖለቲካ ትርፍ ለመሸመት ያሚሙቁለት ለነበሩት ሳይሆን፣ እውነት መስሏቸው ስጋት በውስጣቸው ነዝቶ ለፈሩት ነበር፡፡

ማንም ሰው ግዲታውን ጠንቅቆ እስከተረዳ ድረስ፣ የሚፈልገውን የመሆንም ሆነ የመምረጥ መብት እንዳለው ማወቅ እጅግ በጣም መሠረታዊ እውነታ ነው፡፡ ከሐገሩ ርቆ የሚኖረው ዜጋ፣ እራሱንና ወገኑን የሚረዳበት መንገድ በግልም ይሁን በቡድን በመሰባሰብ የመርዳትና ከጎኑ የመቆም መብት ብቻ ሳይሆን የሞራል ግዴታም አለበት፡፡ ይህ ማለት ግን ትላንት በማምታታትና በማጭበርበር ታሪካቸው እስከዛሬ አብረን እየኖርን በምናውቃቸው ደላላ ቁማርተኞችና የፖለቲካ ሁሊጋኖች፣ ወገኖቻችንን በስማቸው ሊነግዱባቸውና ሊያዘርፏቸው ሲያሰፈስፉ እያዩ ዝም ማለት አይደለም፡፡ ሊጊዜያዊ የፖለቲካ መተቀሚያ ሊጠቀሙባቸው የሚፈልጓቸው ሰዎች ካሉ እንደዚህ በጓሮ በር የሕዝብን ገንዘብ ማባከን ሳይሆን ደሞዝ በግልጽ ከፍለው ያሰሯቸው፡፡

ቢያንስ የጨዋታውን ሕግ እንዲያውቁና ሥነ-ሥርዓአት እንዲማሩና መጀመርያ ያሰልጥኗቸው፡፡ ትላንት በየባቡር ጣቢያውና መንገድ ዳር ትናንሽ ነገር ሲያጭበረብሩ ኖረው ነው፣ አድገው እዚህ የደረሱት፡፡ ነገ ደግሞ ከፍ ብለው ዕድሉን ቢያገኙ እንኳን ሐገሪቷን እናንተን ያሰለፏቿቸውን ጭምር ከመሸጥ አይመለሱም፡፡ ከላይ እንደገለጽኩት ወያኔን መደገፍም ሆነ መቃወም መብት ነው፡፡ እንዲገነባ የምንፈልገውም ሥርዓተ-ማኅበርም በሁሉም አቅጣጫ በልዩነቶቻችን ተከባብረን፣ ፍትኅና ሰላም ሰፍኖ በጋራ እኩል የምንኖርበትን ሐገር ለመገንባት ነው፡፡ እውነተኛ ነጻና ያልተጭበረበረ የሕዝብ ምርጫ ተደርጎ ወያኔን ቢመረጥ ማንም የሕዝብን ውሳኔ ለመቀበል ችግር የለበትም፡፡ ነገር ግን ነገ ለዛ አይነት ዕድል ገና ስላልታደልን ነው እንደ እነዚህ አይነት ሰዎችን አሰለፎ ሚዛን ለመድፋት እየተሞከረ ያለው፡፡ ይህንን አደጋ ለመቃወምና ለመከላከል የመብት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሞራል ግዴታም አለብን፡፡

ኢትዮጵያ እንድታድግና እንድትበለጽግ የማይፈልግ፣ የአባይ ግድብ ቀርቶ እያንዳንዱ ወንዞቻን ለጥቅም እንዳይውሉ የማይመኝ የተቃዋሚ ድርጅቶችም ሆኑ ጤናማ ግለሰብ ይህን የሚቃወም የሐገሪቷ ዜጋ ይኖራል ብዬ አላምንም፡፡ ከአገዛዙና ደጋፊዎቻቸው አንደበት ከምንሰማው በስተቀር እንደዛ ወጥቶ ተቃውሞ የተሰለፈም ሆነ በጽሁፍ አውጥተው አላስነበቡንም፡፡ ነገር ግን ልማት ለፖለቲካ መጠቀሚያ አይዋል፣ ከልማት ጎን የዜጎቻችን ዲሞክራሲያዊ መብት ይከበር ነው እየተጠየቀ ያለው፡፡ ይህንን ጤናማ ጥያቄ ገልብጦ፣ የሕዝብ መብት አይገደብ ካላችሁ፣ አባይ አይገደብ ማለታችሁ ነው፤ ዜጎቻችንን በወስላቶች አታዘርፉ የምትሉ፣ የሕዝብ የልማት እድገት የምትቃወሙ ናችሁ፣ ብለው ያልተባለውን ቀይሮ ማቅረብ አይን ያወጣ ቅጥፈት ነው፡፡

በፖለቲካ አቋማቸው እንኳን ባንደግፋቸው የአንድን ሐገር ባንዲራ ከፊታቸው አስቀምጠው፣ የስንት ሐገር መሪዎችን እየተቀበሉ ከሚያስተናግዱ የአንድን ሐገር መሪ፣ የሰፈር ቁጭ በሉ ወስላቶችን፣ በየቀኑ የማጭበርበር ታሪካቸውን የአገዛዙ ደጋፊዎች እንኳን ጠንቅቀው የሚያውቋቸውን ቺስታዎች፣ እንደ ንዋይ አፍሳሽና አልሚ አድርጎ በማቅረብ ቲያትር መስራት ሕዝብን መናቅ ስለሆነ፣ እንደ አንድ ሐገር ዜጋ ይህንን ማየት ያሳፍራል፡፡ ተመልካችን መናቅ ብቻ ሳይሆን፣ እራሳቸው የመረጧቸውንም የሐገር መሪ ዝቅ አድርጎና አስደርጎ ማስቀመጥ ነው፡፡ ምናልባት ለማስተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ``እኛ ከፈለግን ከመንገድ አንስተን ቤተመንግስት እናስገባሃለን፣ አሊያም እንደ ታምራት ላይኔ ከዙፋን አውርደን ሲያል እንጦሮጦስ ማስገባት መቻላችንን እንድታውቁ``የሚል ካልሆነ? ወይንም እውነትም እንደሚባለው አገዛዙ የሰው ችግር ከሌለበት? በስተቀር ለፖለቲካ ፍጆታ ተብሎ እንደዚህ ቅጥ ያጣ ማጭበርበር እንኳን የውጭ ተመልካችን፣ በራስም ደጋፊ ጭምር መገመት ያስከትላል፡፡ሁሉም የማሰቢያ አዕምሮዋቸው ደንዟል እስካልተባለ፣ በፍርሃት ለጊዜው እራሳቸውን ይደብቁ እንጂ የትም ሰፈር የሚታዘቡና፣ የማመዛዘኛ ህሊና ያላቸው ሰዎች አሉ፡፡

ላለፉት ብዙ ዓመታት እንዳሳለፍነው ተመክሮ ከሆነ፣ የየትኛውንም የፖለቲካ መስመር የሚደግፍ፣ እራሱንም ይሁን ዘመዶቹን ለመርዳት በሚያደርገው ጥረት፣ ለፖለቲካ ቁማርና ሐገርን ለሚጎዳ ተግባር እስካልተጠቀመበት ድረስ፣ ሳንነጋገርም ቢሆን ``በመግባባት`` ሁሉም በራሱ መንገድ ወገኑን እየረዳ ይደጋገፍ ነበር እንጂ፣ ዛሬ ዳር ዳር እንደሚባለው አይነት መጨካከንና አልነበረም፡፡ ሐገር ውስጥ ባለው የኑሮ ውድነት የሚሰቃዩ ወገኖቻችን የተሻለ ሕይወት ከሚኖረው የዲያስፖራው ማኅበረ ሰብ የሚላከው ማንኛውም ዓይነት ዕርዳት ይጠቅማቸዋል፡፡ በድንክዬ አስተሳሰብ ተገድቦ ይህንን መደናቀፍ ምን ማለት እንደሆነ ለማብራራት ቃላት ያጥረኛል፡፡ ቀንና ለሊት እንቅልፍ አጥተው ከባድ ሥራ እየሰሩ፣ እጃቸው እግር እስከሚመስል ያጠራቀሙዋትን ትንሽ ጥሪት፣ ሲደክሙ ለጡረታቸው የቋጠሯትን፣ ለራሳቸውም ይሁን ለቤተሰቦቻቸው የገነቡትን፣ ``እኔ የምደግፈውን ከተቃወምክ? በዚህ እመጣብሃለሁ`` ብሎ ማስፈራራት፣ ይህንን ማፍያዊ አካሄድ ተቀብሎ ደግሞ ማስተጋባት ድንቁርና ብቻ ሳይሆን ወንጀል ነው፡፡ በምድራዊም ይሁን በሰማዩ ያስጠቃል፡፡

እንደዚህ አይነት አካሄድ እንዲጀመር መንገድ መስጠት ሁሉም ቤት ችግር ስላለ የሚጎዳው ሁሉንም ወገን ሲሆን፣ የማይፈለገውን ቀዳዳ በር ከፍቶ ``የሚያነቃው`` ሌላውን አካል ነው፡፡ ዋሽቶና ተደብቆ የተቸገረን መርዳትና ማዳን ሊመሰገን ይገባዋል እንጂ ዋጋው የተገላቢጦሽ ሊሆን አይገባም፡፡ በዚህም መንገድ የወያኔን አገዛዝ እናሰነብታለን ብሎ የሚገምት ካለ ስህተት ነው፡፡

በዚህ ``መግባባትም`` ነው የዲያስፖራው ኅብረተ-ሰብ በውስጡ የተለያየ አመለለካከት ቢኖረውም ፣ በሚያካሂደው የፖለቲካ ትግል፣ የሐገርና የወገን ጥቅም እንዳይጎዳ በጥንቃቄ ይዞ እያቻቻለ ነበር እስካሁን የቆየው፡፡ በግል ፍላጎትና በሐገር ጉዳይ፣ ለጊዜያዊ ቅራቅንቦ ፍጆታና በዘለቄታዊ የወገን ጥቅም መሃል ልዩነቱን በመገንዘብ ነገሮችን አመዛዝኖ ማለፍ እንደ ፍርሃት ወይም አለማወቅ መቆጠር የለበትም፡፡ ይህንን እንደ ፍርሃትና እንዳለማወቅ የሚቆጥሩ ካሉ፣ ነገሮችን የመረዳትና የማመዛዘን ችግር ያለባቸው ይመስሉኛል፡፡ እነዚህ ደግሞ ``የጨዋታን ሕግ`` ስለማያከብሩና በነሱ ምክንያት በሚደርሰው የመልስ ምት፣ አስጠግቶ ያሰለፋቸውንም ቡድን ሽንፈቱን ስለሚያጣድፉለት፣ በየትኛውም ሚዛን ቢመዘን፣ ይህ አካሄድ ላጭር ጊዜ ግር ግር ካልሆነ፣ በረዥሙ ለማየት ከተፈለገ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡ በሁሉም ወገን እንደዚህ አይነት ጨዋታ አበላሾችን፣ ከተቻለ ሕጉንና ደንቡን አስተምሮ በደንብ ገርቶ ማስልጠን፡፡ ይህ የማይቻል ከሆነ? እነሱን አስወግዶ በሌላ ጤናማ ተጫዋች መቀየር ብልህነት ይመስለኛል፡፡ ምናልባት ሌሎቹ ውድ ናቸው እንደ እነዚህ እርካሽ አናገኝም ካልተባለ በስተቀር፡፡ እሱም አይነት ክርክር ቢመጣ፣ ውድና የተሻለ እቃ ይበልጥ ገንዘብ ያስወጣ እንጂ፣ በቀላሉ ከሚሰባበር ቅራቅንቦ ``በተሻለ የረዥም ጊዜ ግልጋሎት ይሰጣል``፡፡

በተረፈ ይህንን አይነት በውጭ ሐገር በምንገኝ መኅበረሰባችን ላይ እየተጀመረ ያለውን አደገኛ አካሄድ፣ ዋጋ ቢያስከፍልም፣ ተባብሮ መግታትና፣ እንዳይቀጥል መከላከል በማንኛውም ሰፈር ያለ ወገኑንና ሐገሩን የሚወድ ዜጋ ሃላፊነት ነው፡፡ ለግል ጥቅም ተብሎ እንደዚህ አይነት አይን ያወጣ ወግንን አደጋ ላይ የሚጥል አካሄድ ባስቸኳይ፣ ተቆጥተንም ይሁን አስቆጥተን ማስቆም አለብን፡፡ የኮሚኒቲ መሪዎች፣ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና ማንም ሃገሩን የሚወድ ዜጋ እንደዚህ አይነት አካሄድ ``ሳይቃጠል በቅጠል`` ብለው የማኅበረሰቡን የጋራ ችግር በጋራ መርዳትና ቶሎ ለመክበር ከተጣደፉ የቀን ጅቦች አደጋ መከላከል ያስፈልጋል፡፡ ምናልባት ``መስበር`` ለጊዜው አስፈላጊ ባይሆንም፣ ቢያንስ ህመሙ ሌላውን እንዴት እንደሚያሳምሙ እንዲሰማቸውና ከእንደዚህ አይነት አፍራሽ **የዘረፋና የማስፈራራት ተግባር እንዲታቀቡ** ማስጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ እምቢኝ አሻፈረን ብለው ካልተመለሱ ችግሩ እራሳቸው ላይ እንደሚብስ ማሳየት የሁሉም ተግባር ሊሆን ይገባዋል፡፡ እንደነዚህ አይነት ግለሰቦች ገንዘብንና ሥልጣንን እንጂ ለማንም ተአሚነት ስለሌላቸውና፣ ለሁሉም ሰፈር ለመጣፈጥ ስለሚፈልጉ፣ ቀን የሰሩትን ማታ ለተቃራኒው እያሾለኩ እንደሚነግዱበት አረጋግጥላችኋለሁ፡፡ ይህ ለሁላችንም የጋራ ሃላፊነት መሆን ሲገባው፣ የማኅበራዊ ግንኙነታቸውንና የግል እቅዶቻቸውን እንዳያበላሽባቸው፣ ወይም ጉዳዩ እነሱን እንደማይመለከታቸውና ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ አድርገው፣ ጥግ ጥጉን ወተት እንደሰረቀች ድመት የሚያደቡትም የጊዜ ጉዳይ እንጂ ነገ የናንተም ችግር ነው ልንላቸው ይገባል፡፡ አጥገባችን ሆነው በጠራራ ፀሐይ ወገኖቻችንን የሚያስፈራሩትን ማስቆም ሳንችል፣ በሺዎች ማይል እርቆ የሚኖረውን ሕዝብ ነጻ እናወጣለን ማለት ቅዠት ነው፡፡ ሕግ ባለበት ነጻ ሐገር ተቀምጣችሁ፣ በአንድ በኩል እከሌ ችግር አደረሰብን፣ አስፈራራን፣ አጭበረን፣ ገንዘብ ቀማን፣ እያላችሁ፣ በጓሮ በር እሮሮ የምታሰሙና በሌላ በኩል፣ ሐገር ውስጥ ባለሥልጣኖች ስለሚያውቅ ይጎዳናል፣ ንብረታችንን ያስወርስብናል እያላችሁ የምትሰጉ መጀመርያ እራሳችሁን ከፍርሃት አንፁ፡፡ በረዥሙ የቃኞችሁ እንደዚህ እንድታስቡና እንድትፈሩ ነው፡፡ ይሳሱ እንጂ በየትም ስፍራ ለፍትኅ የቆሙ ሰዎች እንዳሉ አትርሱ፡፡ ተዋርደናልና፣ ይህንን ብንናገር ሰው ይስቅብናል፣ እነ እከሌን ያስደስታል ...ወዘተ ብላችሁ በራሳችሁ ውስጥ ለመደበቅ አትፍጠሩ፡፡ አትርሱ!! የራሳችሁን ተመክሮ ማካፈል አጥፊውን እጁንና አፉን እንዲሰበስብ ከማድረጉም በላይ፣ ሌሎች ወገኖቻችንን በተመሳሳይ መንገድ እንዳይዘረፉ ይከላከላል፡፡ እንዲህም ስናደርግ ነው በልማት ሽፋን ወገንን ሊዘርፉ የቋመጡ የፖ. ሁሊጋኖችን በጋራ ማስቆም የምንችለው፡፡ ይህንን በአደባባይ እየተካሄደ ያለውን ገሃድ እያየን ዝም ካልን? እነዚሁ አጭበርባሪዎች፣ በሚቀጥለው ዙር መሰሎቻቸውን አሰባስበው፣ ከዲያስፖራ ተደራጅተን ሙስናን ልንዋጋ መጥተናል ብለው ሕዝባችን ላይ እንደሚቀልዱ እርግጠኛ ነኝ፡፡

ኢትዮጵያን እግዚአብሔር ከነልጆችዋ ይጠብቃት !!

ብስራት ኢብሳ (ከሆላንድ)